**ስለ ብኩርና መብት** ዘፍ 25፡27-34፣ 27፡1-27-29፣ 36-37፣ 41

ይህ ትምህርት ስለ ብኩርና መብትና፣ ስለ ሁለቱ የይስሃቅ ልጆች መንፈሳዊ ሕይወት ሁኔታ ይዳሰሳል፡፡

በኩር የሚለው ቃል፣ ቃሉ እንደሚገኝበት ዓረፍተ-ነገር የተወሰነ ተዛምዶ ቢኖራቸውም የተለያየ ትርጉም ይሰጣል፤

ቆላ 1፥15፣ "እርሱ የማይታየው አምላክ አምሳል ነው፤ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤" ይላል፡፡ በዚህ ጥቅስ መሰረት በኩር ማለት፣ "ምንም ዓይነት ፍጥረት ሳይኖር በፊት የነበረ" የሚል ትርጉም አለው እንጂ ከፍጥረት ሁሉ የመጀመሪያው ፍጡር ነው የሚል አይደለም፡፡ ለይስሃቅ በአንድ ጊዜ ከተወለዱት መንትያ ልጆች አንጻር እና "ከማንኛውም ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ የሚወለድ ልጅ ፣ ከማናቸውም የርቢ እንስሳት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚወለድ እንስሳ፤ ከሰሩት የእርሻ/የጉልበትና የአእምሮ ስራ የሚገኝ የመጀመሪያ ምርት/ገቢ ማለት ይሆናል፡፡

ዘፍ 25፡25-26፣ "በመጀመሪያ የተወለደው መልኩ ቀይ፣ ሰውነቱም በሙሉ ጠጕር የለበሰ ነበር፤ ስለዚህ ስሙ ዔሳው ተባለ።[26] ከዚያም ወንድሙ ተወለደ፤ በእጁም የዔሳውን ተረከዝ ይዞ ወጣ፤ ከዚህም የተነሣ ስሙ ያዕቆብ ተባለ። ርብቃ ልጆቿን ስትወልድ፣ ይስሐቅ የሥልሳ ዓመት ሰው ነበር።"

በይስሃቅ 2 ወንድማማች ልጆች መካከል ጥል ያስነሳው የብኩርና መብት ጉዳይ ነበር፡፡ ይሄ የብኩርና መብት ምንና ምን ያካትት ነበር?

1. ዘዳ 21፡15-17፣ አባት/ወላጆች ያፈሩት ቁሳዊ ሀብትና ንብረት ለወራሽ ልጆች ሲከፋፈል በኩር እጥፍ ድርሻ እንዲወርስ ያስችላል፡፡
2. ዘፍ 27፡29፣ 37፣ 49፡3፣ 26፤ በቤተሰቡ አባላት ላይ አለቅነት/ስልጣን፤ የበላይነት፣ ገዥነት፣ የመሪነት ኃላፊነት መሸከም፣ አባት በሞት ሲለይ የአባትን ስፍራ ተክቶ የቤተብ ኃላፊነት ሚና እንዲጫወት ያደርጋል፡፡ አባት በቤተሰብ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ/የተከበረ ከነበረ ልጅም ያንኑ ቦታ የሚያሲዝ ይሆን ነበር፡፡
3. የአባት መንፈሳዊ በረከትም (በነርሱ ዘንድ ለአብረሃም የተሰጠው የተስፋ ቃል) ወራሽ የሚሆነው በኩር ነበር፡፡ ዘፍ 27፡29፣ 28፡4፣ 36-37፣ ሆሴ 12፡6 መንፈሳዊ አለቅነትም የበኩር ነው፡፡

የአባት አምላክ የበኩር አምላክ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን በኩር የእግዚአብሔር ነበር፣ ወይም ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ነበር፡፡ ዘጸ 22፡29፣

ዘፍ 25፡23 ሁለት ወገኖች በማህጸንሽ ናቸው፡፡ ሁለቱም ህዝቦች ከውስጥሽ ተለያይተው ይወጣሉ፤ አንደኛው ከሌላኛው ይበረታል፡፡ ታላቁ ለታናሹ አገልጋይ ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ታናሹ ይበረታል ሲል በተለይም በመንፈሳዊም በረከት እንዲሁም በምድራዊ በረከት ጭምር ነበር (መጥምቁ ዮሐንስ በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናል ተብሎለት ታላቅነቱ የተገለጠው በመንፈሳዊ በረከት ረገድ ነው፡፡) በሁለቱ ልጆች መካከል እያደር እየታየ የመጣው የመንፈሳዊ በረከት ልዩነት ሁኔታ እየሰፋ ሄዶ የአንዱ ጭልም ሲል የሌላው ጎልቶ ታይቷል፡፡

### የሁለቱ ልጆች መንፈሳዊ ሕይወት ሁኔታ

ሁለቱ ልጆች ከአንድ ቤተሰብ የተወለዱ፣ በአንድ ቤት ውስጥ ያደጉና አንድ ቤተሰብ ያሳደጋቸው ናቸው፡፡ ሆኖም ግን እያደጉና ዕድሜያቸው እየጨመረ ሲሄዱ ባህርያቸው እየተለያየ ሄደ፡፡

### የያዕቆብ ያልተገቡ ድርጊቶች፡-

ሀ. ዘፍ 27፡8-13፣ ለአባቱ ኤሳው ነኝ በማለት መዋሸቱ ኃጢአት ቢሆንም እናቱ ርብቃ አስፈላጊ ባልሆነ መገፋፋት ገፋፍታ ግድ ስላለችው ወላጅነቷን አክብሮ እርግማን ስለ ማስከተል አለማስከተሉ ከኔ ይልቅ እርሷ ልታውቅ ትችላለች በሚል ይመስላል፣ እየከበደውም ቢሆን እንደ ታዘዛት ያሳያል እንጂ ሃሳቡ ከራሱ ልብ የመነጨ/የታቀደ አይደለም፣ እንዲያውም ይሄማ መርገም ስለ ሚያስከትልብኝ ላደርገው አይገባም በማለት ኃጢአት ማድረግ መርገምን በራስ ላይ ማምጣት እንደሆነ ተናግሮ በመጠንቀቅ እናቱን ይቅርብኝ ቢላትም እንኳ ያለችውን እንዲያደርግ መጫንዋን ስላላቆመች ይሄ የእርሱ ጥፋት ነው ብሎ መፈረጅ ያስቸግራል፡፡ ርብቃ ይህን በማድረጓ የተከሰተው ችግር ቤተሰቡን ሁሉ እንዴት እንዳመሰ በኋላ እናያለን፡፡

ለ. ዘፍ 30፡41-42፣ ከላባ በጎች ጥሩ/ሻል ያለ ቁመና ያላቸውን ብቻ መርጦ ለእርሱ ግልገሎች እንዲወልዱ ማድረጉ አግባብ አይደለም (ተለቅ ያሉትን አነስ ካሉት ሳይመርጥ ማስጠቃት ነበረበት)፡፡

ሐ. ዘፍ 31፡20፣ 31 ያዕቆብ ከላባ ዘንድ ወጥቶ ወደ አባቱ አገር ለመመለስ በወሰነ ጊዜ ለላባ ሳይነግረው ጉዞ መጀመሩ (ይህን ለማድረግ የሚያነሳሳ ምክንያት ላባ ያዕቆብን የሚጎዳ ብዙ ነገር ስላደረገ ልያና ራሔል የወለዱዋቸውም ልጆች ጭምር ይወስድብኛል ብሎ ስለ ፈራ እንደነበር አስረድቷል፡፡)

ያዕቆብና ቤተሰቦቹ ይህና ያ ክፉ ወይም መልካም ድርጊት አደረጉ የምለው ዛሬ እኛ ባለንበት ዘመን ግልጽ የሆነ የአኗኗር መመሪያ የሚሆነን የእግዚአብሔር ቃል ስለ ተሰጠን ከዚህ ቃል አንጻር በማየት ነው እንጂ በእነርሱ ዘመን እንዳሁኑ ጊዜ ያለ (የብሉይ ኪዳንም ሆነ የአዲስ ኪዳን) የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል እንዳልነበረ መርሳት የለብንም፡፡

## የያዕቆብ መልካም ድረጊቶች፡-

**ያዕቆብ** ጭምት (ረጋ ያለ) ከድንኳን አካባቢ የማይርቅ ሰው ነበረ፣ ይለዋል የእግዚአብሔር ቃል፡፡ ዘፍ 25፡27

- ብኩርናን ያከብርና በብርቱ ይፈልግ ነበር፣ በአንድ ጊዜ መብል መግዛት ብቻ ሳይሆን ብኩርና ለማግኘት ብዙ ዋጋ ከፍሏል፣ ሕይወቱን እስከማጣት ደርሶ ከናት አባቱ ተለይቶ ተሰዷል፣ ለረጅም (20) ዓመታት የአጎቱ ላባ የርቢ እንስሳት ጠባቂ ሆኗል፡፡ ይህን ያደረገው በእግዚአብሔር ፊት የከበረን ነገር ለይቶ የሚያውቅ ሰው ስለነበር ነው፡፡ የሚጠማው፣ ባለ ኃይሉ የሚዋጋለትና የሚተጋለት አንድ ቁም ነገር ነበረው፣ ያም ነገር ብኩርና ነበር፡፡ ያ የብኩርና በረከት እግዚአብሔር ለእርሱ ያየለት ነበር፡፡ ያዕቆብ ከወንድሙ ይልቅ እንዲበረታና የበኩር ድርሻ እንዲወርስ እግዚአብሔር መርጦት ነበር፡፡ ዘፍ 25፡23፣ ሮሜ 9፡11
- ማግኘት የፈለገውን ቁም ነገር ለማግኘት ማናኛውም ዋጋ ቢከፍልም እስከ ፍጻሜው ጸንቶ ይሰራ ነበር፡፡ ብኩርናን ለማግኘት 20 ዓመታት ተሰደደ፣ ራሄልን ለማግኘት 7 ዓመት ላባን ለማገልገል ተዋውሎ ሳለ ላባ እንደገና 7 ዓመታት ስላስጨመረው ለ14 አመታት ደክሞ ቢሰራም ከምንም አልቆጠረውም (እንደ ጥቂት ቀናት አየው)፡፡ ዘፍ 29፡19-20፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሲታገል አድሮ ሾልዳው ተጎድቶ በእግሩ መራመድ እስከ ሚከብደው ደርሶ እያለ፤ ካልባረክኸኝ አልለቅህም በማለቱ እግዚአብሔርም መጨረሻ ላይ ባርኮት ነው የሄደው፡፡ በያዘው መልካም ዓላማ የሚጸና ሰው ነበር፡፡(ዘፍ 32፡24-29) በጊዜያዊ ነገር ሳይሆን በዘላቂ (ቁሳዊና መንፈሳዊ) በረከት ላይ ትኩረት ያደርግ ነበር፡፡
- ያዕቆብ የወላጆቹን ፈቃድ/አድርግ ያሉትን ያደርግ ነበር፡፡ እናቱ ርብቃ አባቱ እንዲመርቀው አድርግ ብላ የተናገረችውና ኤሳው ሊገድለው እንዳቀደ ስትሰማ ሽሽ ያለችው 27፡8-14፣ 42-44፣ አባቱ ይስሃቅ ያላባን ልጅ እንዲያገባ የተናገረውን ማድረጉ፣ 28፡1-5፣7፤

- የአጎቱ የላባ ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ አግኝቷት ሲያውቃት ሳማትና ድምጹን ከፍ አድርጎ ማልቀሱ ቢያንስ የዘመድ ፍቅር እንደ ነበረው ይገልጻል፤ ዘፍ 29፡9-11፣
- ዘፍ 30፡32ና ዘፍ 31፡10-12 በማስተያየት ዝንጉርጉርና ሽመልመሌ በትር በሚጠቁት እንስሳት ፊት ያደርግ የነበረው፣ አንዳንዶች እንደ ጥንቆላ ዓይነት አሰራር አድርጓል ይሉታል፡፡ ነገር ግን መጠንቆሉ ሳይሆን እግዚአብሔር በአጎቱ ላባ የተበደለ መሆኑን አይቶ ሊረዳው በህልም በመልአኩ አማካኝነት ያሳየው ስለሆነ ነው፡፡ ሁለቱ ጥቅሶች መደዳ ባይጻፉም ይዘታቸው የተያያዙ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ያዕቆብ ከመልአክ የተነገረው ነገር ሳይናገር ቆየት ብሎ ለሚስቶቹ በኋላ ገልጦታል፡፡
- ዘፍ 32፡13-16፣ ከወንድሙ ጋር በተጣሉበት ጉዳይ ዔሳውን በማረጋጋት ሰላም ለማስፈንና በደህና እንዲቀበለው ለማድረግ 580 (ግልገሎች ጭምር) የርቢ እንስሳት እጅ መንሻ/ስጦታ አዘጋጅቶ ከፊቱ አስቀድሞ ኤሳው ወዳለበት እንዲሄድ ማድረጉ፣ (ቢጣላኝ በዚህ ወይም በዚያ ሁኔታ እመክተዋለሁ/ እበቀለዋለሁ ብሎ በማቀድ ፈንታ ከቁጣው እንዲያለዝበው በማሰብ ማድረጉ፡፡)
- ዘፍ 32፡4፣ 18፣ 20፤ 33፡5፣13፣14፣ ያዕቆብ ከፊት ለፊቱ የስጦታ እንስሳት እየነዱ ኤሳው ወዳለበት አንዲሄዱ ያደረጋቸው የእንስሳቱ ጠባቂዎችን በእነዚህ ስድስት ጥቅሶች 6 ጊዜ ለጌታዬ ለዔሳው አገልጋይህ ያቆብ ከኋላችን እየመጣ ነው ማለትን አትርሱ ብሎ ማስጠንቀቁ ትህትናውን የሚያሳይ ነው፡፡

“እንዲህም ብሎ አዘዛቸው፤ “ጌታዬን ዔሳውን እንዲህ ትሉታላችሁ፤ ‘አገልጋይህ ያዕቆብ እንዲህ ብሎአል በሉት፤ “ከላባ ዘንድ ተቀምጬ እስከ አሁን ድረስ እዚያው ኖርሁ፤…”

- ዘፍ 33፡3፣ ወንድሙ ኤሳው ወደ እርሱ እንደተቃረበ ያዕቆብ 7 ጊዜ ወደ መሬት ለጥ ብሎ እጅ መንሳቱ፤
- ዘፍ 33፡4፣ ለብዙ ዓመታት ተለየያይተው ኤሳው ጋር እንደ ተገናኙ ተቃቅፈው መላቀሳቸው፡፡ (ለ2ቱም የመልካም ድርጊት ነጥብ የሚያስገኝ ነው)፡፡
- ዘፍ 33፡10፣ ያዕቆብ ወንድሙ ጋር ተገናኝተው ለኤሳው ያቀረበለትን 580 የርቢ እንስሳት እጅ መንሻ፣ እኔ የሚበቃኝ ያህል ስላለኝ ያንተን ለራስህ አድርገው ባለው ጊዜ የተናገረው የሚመስጥ የትህትና ቃል፡፡

“ያዕቆብም፣ “የለም፣ እንዲህ አይደለም፤ በአንተ ዘንድ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ፣ እጅ መንሻዬን ተቀበል፤ በመልካም ሁኔታ ተቀብለኸኝ ፊትህን ማየት መቻሌ ራሱ፣ የእግዚአብሔርን (ኤሎሂም) ፊት የማየት ያህል እቈጥረዋለሁ።”

- ዘፍ 33፡11፣ ያዕቆብ ያቀረብኩልህን እጅ መንሻ እባክህ ተቀበለኝ በማለት አጥብቆ ስለ ለመነው፣ ኤሳው እጅ መንሻውን ተቀበለ፡፡ (ከልቡ መስጠት እንደ ፈለገ ያሳያል)

**ያዕቆብ ከእግዚአብሔርና መላዕክቱ ጋር የተገናኘባቸው ጊዜያትና ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት ከየት ተማረ በሚያሰኝ ሁኔታ ያውቅበት እንደ ነበር የሚያሳዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፡ -**

1. ዘፍ 28፡10-15፣ ያዕቆብ ከኤሳው ሸሽቶ ወደ ላባ ሲሄድ እግዚአብሔር ሎዛ ይባል በነበረው ስፍራ ተገልጦለት እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ብሎ ለአብረሃም የሰጠው የተስፋ ቃል ለእርሱና ለዘሩ እንሚሰጥ በማረጋገጥ በብዙ በረከት ባረከው፡፡

- ዘፍ 28፡18-19፤ እግዚአብሔር ጋር የተገኛኘበትና የተስፋ ቃል የተቀበለበት ስፍራ መታሰቢያ እንዲሆን ተንተርሶት ያደረው ድንጋይ አንስቶ በማቆም ሐውልት ሰራበት፤ በአናቱም ላይ የወይራ ዘይት አፈሰሰበት፡፡ ቦታውም የእግዚአብሔርን ውለታ የሚያስታውስበት ስም በማውጣት ቤቴል (የእግዚአብሔር ቤት) ብሎ ሰየመው፡፡
- ዘፍ 28፡20-22፣ እግዚአብሔር በሚያደርግለት/በሚሰጠው ለሰው ሁሉ በሚያደርገው መደበኛ በረከት ማንም ሳይገፋፋው ወይም ሳይጠይቀው እግዚአብሔርን መልሶ ለማገልገል፤ የሚቻለውን

ያህል ለባለውለታው መልካም ምላሽ ለመስጠት ዝግጁና ፈጣን ሆኖ ቃል መግባቱ፡፡
እግዚአብሔር ከሰጠው ነገር ሁሉ 1/10ኛው ለአግዚአብሔር ለመስጠት ራሱን ያዘጋጀና ቃል የገባ የመጀመሪያ ሰው ነው፡፡ ይሄ ለአንድ ዓመት ሰርቶ ካገኘው ሳይሆን ለሁሌ መሆኑ ነው፡፡ (አብረሐም ከግረከው ምርኮ 1/10ኛ ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው የሰጠው)

2. ዘፍ 31፡10-12፣ የእግዚአብሔር መልአክ በህልም በጎቹን እንዴት ማስጠቃት እንዳለበት ነገረው፡፡
3. ዘፍ 31፡3፣ 17፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሆነ ነግሮት ወደ አባቶቹ አገር እንዲመለስ መራው፡፡
4. ዘፍ 32፡1-2፣ ያዕቆብ ከላባ ዘንድ ወጥቶ ወዳገሩ ለመመለስ ጉዞ እንደ ጀመረ መንገድ ላይ የእግዚአብሔር መላዕክት ተገናኙት፡፡ እርሱም ያንን ስፍራ "ይህ የአግዚአብሔር ሰፈር ነው" አለ፤ የቦታውም ስም መሃናይም ብሎ ጠራው፡፡ መሃናይም ማለት 2 ጎራ (ካምፕ) ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሰራዊት እና የያዕቆብ ሰራዊት 2ቱ ጎራ የተገናኙበት ስፍራ ለማለት ነው፡፡
5. ዘፍ 31፥22-24፣ አጎቱ ላባ የያዕቆብ መኮብለል ሲሰማ ዘመዶቹን ሰብስቦ ለ7 ቀናት ተከታትሎ ሊደርስበትና ሊያጠቃው ሲል እግዚአብሔር ተከላከለለት፡፡ “ከዚያም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ለሶርያዊው ለላባ በሕልም ተገልጦ፣ “ያዕቆብን፣ ክፉም ሆነ ደግ፣ እንዳትናገረው ተጠንቀቅ” አለው። ”
6. ዘፍ 32፡24-30፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሲታገል አደረና ባረከው፡፡
   - ከእግዚአብሔር ጋር ሲታገል ያደረበት ስፍራም ጵኒኤል የሚል መታሰቢያ ስም አወጣለት፡፡ (ጵኒኤል፡- የእግዚአብሔር ፊት ማለት ነው)

“ስለዚህ ያዕቆብ፣ “እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) ፊት ለፊት አይቼ እንኳ ሕይወቴ ተርፋለች” ሲል፣ የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል አለው።”

   - ዘፍ 33፡20፣ ከኤሳው ጋር ታርቀው ከተሰነባበቱ በኋላ ድንኳኑ የተከለበት ሴኬም ላይ መሰዊያ አቁሞ "ኤል ኤሎሄ እስራኤል" አለው፡፡(ትርጉሙ፡- የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር/የእስራኤል አምላክ ኃያል የሚል)

ነገር ግን በሴኬም ጥቂት ጊዜ እንደ ቆዩ የሴት ልጁ የዲና ወንድሞች ሰምዖንና ሌዊ እህታቸው በመደፈሯ በሴኬም ከተማ ነዋሪዎች ላይ ከባድ ጥቃት ስለ ፈጸሙ ያዕቆብ በአካባቢው ነዋሪዎች አጸፋዊ ጥቃት ይፈጸምብናል በሚል ሰግቶ ነበር፡፡

7. ዘፍ 35፡1፣ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ለያዕቆብ ተገልጦለት ሴኬምን ለቆ ወደ ቤቴል ሄዶ በዚያ እንዲኖር ነገረው (ምሪት ሰጠው)፡፡

   - ዘፍ 35፡1-3-4፣ ያዕቆብ ለቤሰቦቹና አብረውት ለነበሩት ሁሉ ለእግዚአብሔር መስዋዕት ለማቅረብ ወደ ቤቴል ስለ ምንወጣ ጣኦታትና ጸያፍ ነገሮችን ሁሉ አስወግዱ አለ፡፡

“ስለዚህ በእነርሱ ዘንድ የነበሩትን ባዕዳን አማልክት ሰብስበው፣ የጆሮ ጉትቾቻቸውን አውልቀው ለያዕቆብ ሰጡት። ያዕቆብም ወስዶ ሴኬም አጠገብ ካለው ወርካ ዛፍ ሥር ቀበራቸው።”

እግዚአብሔርን ለማምለክ ከመውጣቱ በፊት ቤተሰቦቹ እግዚአብሔር የማይፈልጋቸው ጣዖታትን

አስወግደው ንስሃ ገብተው ልባቸውን ወደ እግዚአብሔር አዘንብለው እንዲያመልኩት አድርጓል፡፡

8. ዘፍ 35፥5፣ “ያንንም ቦታ ለቀው ሄዱ፤ እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) በዙሪያቸው በነበሩት ከተሞች ሁሉ ላይ ፍርሀትና ድንጋጤ ስለ ለቀቀባቸው ያሳደዳቸው አልነበረም።” (በዚህም ጊዜ በዙሪያቸው የነበሩት ከተሞች ነዋሪዎች ሊያጠቁን መምጣታቸው አይቀርም፡፡ እነርሱ ብዙዎች ናቸው፤ እኛ

ግን ጥቂቶች ስለሆንን አንቋቋማቸውም በማለት እስራኤል ስጋት ሲይዘው እግዚአብሔር በእነርሱና በጠላቶቹ መካከል ጣልቃ ገብቶ አዳናቸው፡፡)

9. ዘፍ 35፡11-15፣ ያዕቆብ በቤቴል መሰዊያ ሰርቶ መስዋዕት ካቀረበ በኋላ እግዚአብሔር እንደገና ተገልጦለት ባረከው፡፡

- ዘፍ 14-15፣ ያዕቆብ እግዚእብሔር (ኤሎሂም) ከእርሱ ጋር በተነጋገረበት ስፍራ የድንጋይ ሐውልት አቆመ፤ በሐውልቱ ላይ የመጠጥ ቍርባን አፈሰሰ፤ ዘይትም አፈሰሰበት። [15] ያዕቆብም፣ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከእርሱ ጋር የተነጋገረበትን ስፍራ ቤቴል ብሎ ጠራው።

- ዘፍ 32፡10፣ እግዚአብሔር ያደረገለት ቸርነትና ያሳየው ታማኝነት ታላቅነት በማሰብ ያን ያህል እንዲባርከው የተገባው እንዳልነበረ በመናገር ስለ ሰጠው በረከት እግዚአብሔርን አከበረ፡፡ ዮርዳኖስን ስሻገር በእጄ ከነበረው በትር በስተቀር ምንም አልነበረኝም፤ አሁን ግን ሁለት ሰራዊት ሆኛለሁ፡፡ (ዘፍ 32፡7)
- 31፡3፣ 17፣ 35፡1፣ 6-7፣ እግዚአብሄር አድርግ ያለውን የሚያደርግ ሰው ነበር፡፡ ወደ አባቱ አገር እንዲመለስ ተናገረው፡፡ ወንድሙ ሊገድለው ይፈልግ እንደነበረ እያወቀ ለመመለስ ጉዞ ጀመረ፡፡ ከሰፈረበት ሴኬም ወደ ቤቴል እንዲሄድ ስለ ሲነግረው ወዳለው ቦታ ሄደ፡፡
- 31፡37-39-42፣ አውሬ የሰበረው እንስሳ እንኳ ለላባ ይተካ ነበር፣ በቀንም ሆነ በሌሊት የተሰረቁት እንስሳት ለላባ ይከፍል ነበር፡፡ አጎቱ ላባ ብዙ ቢበድለውም ለ20 ዓመታት ታግሶ አገልግሎታል፡፡

(እንዴት ዓይነት ከባድ ኑሮ እየኖረ እንደነበረ እንዲህ ሲል ገልጦታል፡፡ ዘፍ 31፡38-40፣ ሃያ ዓመት አብሬህ ኖሬአለሁ፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከመንጋህ አንድ ጠቦት እንኳ አልበላሁም። [39] አውሬ የሰበረውንም ቢሆን እተካ ነበር እንጂ፣ ትራፊውን ለምልክትነት አምጥቼ አላውቅም፤ በቀንም ሆነ በሌሊት የተሰረቁትን ሁሉ ስታስከፍለኝ ኖረሃል።[40] ቀን በሐሩር ሌሊት በቍር ተቃጠልሁ፤ እንቅልፍም በዐይኔ አልዞር አለ፤)

- 31፡30፤32፣ የቤተሰቡ አባላት ክፉ ድርጊት ሲፈጽሙ ያወግዝ ነበር፡፡ የጣዖት ምስል በመስረቅ እንዲህ ክፉ ነገር የሰራ ማንም ቢሆን ይሙት አለ፣ ራሄል ቢንያምን ስትወልድ ምጥ ከብዶባት የሞተችው በዚህ ምክንያት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ (ዘፍ 35፡16-19)

ዘፍ 34፡25-31፣ ልጆቹ ሰምዖንና ሌዊ በከነአናዊያንና ፌርዛውያን ላይ በእህታቸው ዲና መደፈር ምክንያት ያልተመጣጠነ ከባድ እርምጃ በመውሰዳቸው ማውገዙ የአካባቢው ሰዎች ተባብረው ቢነሱብን እኛ ጥቂቶች ስለሆንን ቤተሰባችንን ሁሉ ያጠፉ ነበር ከማለት አኳያ ብቻ ሳይሆን ብዙ ቆይቶ በእርጅና ዘመኑ እንኳ የቁጣና ጭካኔ ስራቸው ከንክኖት ልጆቹን ሲመርቅ ቀጥቷቸዋል፡፡ ዘፍ 49፡5-7

**ከላይ እንደ ተዘረዘረው የቀድሞው ያዕቆብ በኋላ ግን እስራኤል በርካታ መልካም ድርጊቶች የፈጸመ መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ስለ ሚመሰክርለት እኛም የአሁኑ ዘመን የወንጌል አማኞች ከእርሱ ልንማራቸው ከሚገቡን ነገሮች አንድ ያህሉን መጥቀስ የግድ ይላል፡፡**

1. ያዕቆብ እግዚአብሔር ለአርሱ ተገልጦ ያበረታታበት፣ ምሪትና የተስፋ ቃል የሰጠበት በተለያየ መንገድ የረዳበት ስፍራ እንዴት ያከብር እንደ ነበረ በማየት፣ እግዚአብሔር ለኛ ተስፋ የሰጠውን፣ በመንፈሱ ያነቃቃበትን፣ የፈወሰበትን፣ በተለያየ መንገድ የረዳበትን ስፈራና ቀን ሀውልት ባንሰራም ማስታወሻችን ላይ እንኳ ጽፈን ይዘን በየጊዜው ውለታውን በማስታወስ ማክበርና ማመስገን ልማድ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ እኛ የምናሳየው በአብዛኛው ማጉረምረም፣ ማማረር በእምነት በማደግ ፈንታ ይበልጥ ተጠራጣሪ መሆንን … ወዘተ ፈጽመን ልናርቃቸው ይገባል፡፡
2. ክርሰቶስ ኢየሱስ አላፊ የሆኑ ምድራዊ ነገሮች ብቻ ሳይሆን ለእኛ በአሰቃቂ ሁኔታ የሕይወት መስዋዕትነት ከፍሎ ያዳነን ስለሆነ፣ ሰርተን ካገኘነው ነገር አቅማችን በፈቀደው መጠን ደስ እያለን ማንም ሳይገፋፋን አስራትና መባን ሌሎችም ስጦታዎችን ለመስጠት መነሳሳት፡፡

3. ያዕቆብ ከአባቶቹ አገር ከቤርሳቤህ ወጥቶ ወደ አጎቱ ላባ ሄዶ ከዚያም ተመልሶ አባታቸው ይስሃቅ በመሞቱ ከዔሳው ጋር እስከ ቀበሩበት ጊዜ ድረስ እግዚአብሔር ራሱ ለያዕቆብ 5 ጌዜ፣ የእግዚአብሔር መላዕክት 2 ጊዜ የተገለጡለትና የተገኛኙት ሲሆን እግዚአብሔር አደጋ ሊጥሉበት ከነበሩ ሰዎች ያዳነው 2 ጊዜ ነው፡፡ እኛ ግን እግዚአብሔር አልፎ አልፎ ሳይሆን ሁል ጊዜ በውስጣችን ከእኛ ጋር ስለሚኖር በጸጋው ከሚገባን በላይ እያደረገልን ስላለ፣ ከያዕቆብ ይልቅ አብልጠን ልናከብረው ልናመሰግነው ይገባናል፡፡
4. ያዕቆብ የከበረ መንፈሳዊ ብኩርናና የእግዚአብሔር በረከት መፈለግ ጀምሮ እጁ እስከ ሚገባ ድረስ ጸንቶ ይቀጥል እንደ ነበረ እኛም ቶሎ እጃችን ባልገባ በረከት ተስፋ በመቁረጥ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ትተን የበረከታችን ጠላቶች የሆኑትን የጭለማው ኃይላትንና ኃጢአትን በመዋጋት ለመቀደስና ለእያንዳንዳችን በከፈተልን የአገልግሎት በር ማድረግ የምንችለውን ሁሉ በትጋት በማድረግ ጸንተን መቀጠል ይኖርብናል፤

እንዲህ በጸና ትጋት በፊቱ ጉድ ጉድ ስንል እግዚአብሔር እስራኤልን ከበድ የሚለው ማንኛውም ችግር በገጠመው ጊዜ ከተፍ እያለ ይረዳውና ይዋጋለት እንደ ነበረ ለእኛም እንደዚያው ያደርጋል፡፡

**የዔሳው ተገቢ ያልሆኑ ድርገቶች**

ኤሳው ብኩርና ምንም እንደ ማያደርግለት አቅልሎ/ዝቅ አድርጎ በማየት በመሃላ በማረጋገጥ ለያዕቆብ እንደ ሸጠለት መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያናገራል፡፡

ዘፍ 25፥32፣ "ዔሳውም፣ "እነሆ፣ ልሞት ደርሻለሁ፤ ታዲያ ብኵርናው ምን ያደርግልኛል!" አለ።" (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ዘፍ 25፥33፣ "ያዕቆብም ዔሳውን፣ "እንግዲያማ፣ አስቀድመህ ማልልኝ" አለው፤ ስለዚህም ማለለት፤ ብኵርናውንም ለያዕቆብ ሸጠለት።"

ዘፍ 25፥34፣ "ያዕቆብም ለዔሳው እንጀራና የምስር ወጥ ሰጠው፤ እርሱም ከበላና ከጠጣ በኋላ ተነሥቶ ሄደ። ዔሳው ብኵርናውን እንዲህ አድርጎ አቃለላት።"

Heb 12:16፣ (NIV) "See that no one is sexually immoral, or is godless like Esau, who for a single meal sold his inheritance rights as the oldest son." (ዕብራውያን 12፡16-17ን የእንግሊዝኛ NIV ና NET ትርጉሞች አምላክ የለሽ ኤሳው ብለው ተረጉመውታል፡፡)

- ብኩርናን እጅግ በርካሽ ዋጋ በመሃላ በማረጋገጥ በመሸጡ፤ በእጁ የነበረው የከበረ ነገር ተጠንቅቆ አልያዘም ለዚህ ምክንያቱ ዘፍ 26፡1 ምናልባት በዚህ ጊዜ የይስሀቅ የእንስሳትና የእህል ሀብት በድርቁ ምክንያት በመቀነሱ ሊሆን ይችላል፡፡ ቁሳዊው ሀብት ሲመናመን መንፈሳዊውን በረከት እንደበኩር መውረስ ለርሱ ቀላል ሆኖ ታይቶ ሊሆን ይችላል፡፡ ያዕቆብም ብኩርናህን ሽጥልኝ ብሎ የጠየቀው ኤሳው ብኩርናውን አናንቆ ሲናገር ሰምቶ ሊሆን ይችላል፡፡ ያዕቆብ ለኤሳው ቀይ ወጥ በነጻ እንኳ ያለላበት፣ ኤሳውም ለመግዛት የተስማማበት ምክንያት ቀደም ሲል ኤሳው አድኖ በሚያመጣው ነገር ያካፍለው የነበረ ባይሆን ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በሁለቱ መሀከል ጥሩ ግንኙነት፣ መተሳሰብ/መደጋገፍ የነበረ ቢሆን ያዕቆብ ወጥ የመሸጥ ጥያቄ አያነሳም ነበር፡፡
- ኤሳው ያማረው ቀይ ወጥ እንጂ ሌላ ካለመሆኑ የተነሳ ካልሆነ በቀር ከይስሀቅ ቤት ከርብቃ እጅ የሚቀመስ ነገር ጠፍቶ በረሀብ ለመሞት ደርሶ ነበር ለማለት ይከብዳል፡፡ ያለበቂ ምክንያት ለጊዜው ላማረው ያዕቆብ ላዘጋጀው ቀይ ወጥ ሲል ብቻ ብኩርናውን መሸጡ እንጂ ህይወቱን ለማትረፍ ቢሆን ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስ ብኩርናውን አቃለለ አይለውም ነበር፡፡ ስለዚህ ለጊዜያዊ ነገር ሲል ዘላቂ መንፈሳዊ በረከት መሸጡ ብቻ ሳይሆን ቆይቶ ከጊዜ በኋላ እንኳ ብኩርናዬን

በመሸጡ ተጸጸትኩ ብሎ ለወንድሙ ሲናገር ስለማይታይ ትኩረቱ በጊዜያዊ ነገር ላይ መሆኑ ያስረዳል፡፡

- ብኩርና ኤሳው ተስማምቶ የሸጠውን መሆኑን አባቱ ስላላወቀ ከረፈደ በኋላ መልሶ ፈለገው፡፡ የሚያደርገውን ነገር አመዛዝኖ የማይጀምር፣ በተዋዋለውም ውል (በያዘው አቋም) የማይጸና ሰው ነበር፡፡ ብኩርናዬን አታሎ ወሰደብኝ ያለው ራሱ ፈልጎ ምን ያደርግልኛል ብሎ በመሃላ የሸጠው መሆኑን ረስቶት ይሆን፡፡ ይስሃቅ ኤሳው መስሎት ለያዕቆብ የባረከው ባርኮት ለበኩር የተገባ ባርኮት ነው፡፡ ኤሳው ግን ብኩርናና አንኳር ምርቃት ለያይቶ አያቸው፡፡ ዘፍ 27፡36 መጽሐፍ ቅዱስ ግን ምርቃቴ ወሰደብኝ ብሎ ያለቀሰበት ነገር ያው ብኩርና (የብኩርና መብት) መሆኑን ይናገራል፡፡

*ዕብ 12፡16-17፣ ለአንድ ጊዜ መብል ሲል ብኵርናውን እንደ ሸጠው እንደ ዔሳው ማንም ሴሰኛ ወይም እግዚአብሔርን የማያከብር ሆኖ እንዳይገኝ ተጠንቀቁ።[17] በኋላም ይህንኑ በረከት ሊወርስ በፈለገ ጊዜ፣ እንደ ተከለከለ ታውቃላችሁ፤ በረከቱን በእንባ ተግቶ ቢፈልግም መልሶ ሊያገኘው አልቻለም።*

- ሁኔታው በዚህ ደረጃ ላይ እያለ ኤሳው ያዕቆብን በጭካኔ ለመግደል ወስኖ ምቹ ጊዜ ይጠባበቅ የነበረ መሆኑና፣ ያዕቆብ እናቱ እንዲዋሽ ስትገፋፋው ይኼማ መርገም ስለ ሚያስከትልብኝ እንዴት እዋሻለሁ ብሎ ከተሟገተው ጋር ሲነጻጸር በሁለቱ ወንድማማቾች መካከል ያለው ልዩነት ምን ያህል የሰፋ እንደ ሆነ ያሳያል፡፡
- ኤሳው በሕይወት ዘመኑ እግዚአብሔርን የማምለክና ክብር የመስጠት ዝንባሌ የነበረው መሆኑን የሚያሳይ በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ ምንም የተመዘገበ ድርጊት የለም፡፡
- ኤሳው ወላጆቹን በማክር ፈንታ ራሱ የፈቀደውን ያደርግ ነበር፡፡ (ዘፍ 27፡46፣ 28፡8-9፣) ኤሳው እናቱን አክብሮ እንደ ማይታዘዛት እርግጠኛ ባትሆን ኖሮ በሁለቱ ልጆችዋ መካከል የተፈጠረው አምባጓሮ በማግባባት ለመፍታት ትሰራ ነበር እንጂ የያዕቆብ መሰደድ ብቸኛ መፍትሄ አድርጋ አትወስደውም ነበር፡

**የኤሳው መልካም ድርጊቶች**

- የኤሳው 2ቱ ኬጢያዊያን ሚስቶች ወላጆቹ ያዘኑባቸው መሆኑን ሲያውቅ የወሰደው የማስተካከያ እርምጃ በመልከምነት የሚታይ ነው፡ ዘፍ 28፡8-9 (የአብርሐም ልጅ እስማኤል የወለዳት ማዕሌትን ያገባው ወላጆቹን ቅር በተሰኙበት ነገር እንድታግዝ ይመስላል)፡፡
- አባቱ ይስሃቅ የሚወደውን ለማዳ ያልሆኑ እንስሳትን በማደን አሳምሮ በማዘጋጀት መመገቡ፡፡
- ዘፍ 33፡4፣ ያዕቆብ ከላባ ዘንድ ተመልሶ በመጣ ጊዜ ኤሳው ከያዕቆብ ጋር በቅርበት ሲተያዩ ሊገናኘው ወደ እርሱ ሮጦ ሄዶ ማቀፉና በአንገቱ ላይ ተጠምጥሞ መሳሙና መላቀሳቸው፡፡
- ኤሳው ከያዕቆብ ተሰናብቶ ወደ መጣበት ሊመለስ ሲል ከእርሱ ጋር ከነበሩት ሰዎች ጥቂቶቹን ልተውልህ ማለቱ፤

ይስሀቅና ርብቃ ልጆቻቸውን ከአንዱ ሌላውን አበላልጠው ይወዱ ነበር፤ ዘፍ 25፡28፡፡ ሁለቱም ወላጆች ኤሳውም ሆነ ያዕቆብ ከአብራካቸው የወጡ ስለሆኑ ከሁለቱ የትኛውም ቢባረክ ያው ልጃቸው ስለሆነ እነርሱም የበረከቱ ተጠቃሚዎች ይሆኑ ነበር ማለት ነው፡፡

ርብቃ ያዕቆብን ለመርዳት ብላ ያደረገቻቸው ነገሮችና ያስከተሉት ቤተሰቡን ሁሉ ያመሰ ችግር፡-

- ያዕቆብን ኤሳው ነኝ ብለህ አባትህን ዋሸው ብላ አጥብቃ ይዛዋለች፤
- የያዕቆብ ውጫዊ ገጽታውን በመለወጥ ኤሳውን እዲመስል አድርጋለች፤ የሰራቸውም ምግብ ኤሳው ከአደን አምጥቶ ለአባቱ የሚመግበው ምግብ ዓይነት የሚመስል ምግብ ሰራች፡፡

- ያደረገቻቸው ነገሮች በኋላ በቤተሰቡ አባላት ሕይወት ላይ ምን ውጤት እንደ ሚያስከትሉ አለማሰቧ፣
- ያዕቆብን በአባቱ ካስመረቀች በኋላ እንኳን ለባልዋ ለይስሃቅ የተሰራው ስህተት አስታውቃው ቢሆን ኖሮ ወንድሙ ያዕቆብ ምርቃቱን እንደ ወሰደበት ሳይነገረው ኤሳውንም ለመመረቅ ዝግጁ እንዲሆን ባለማድረጓ፣ ይስሃቅ የበኩር ልጄን መርቄ ጨርሻለሁ ብሎ በተዝናናበት ድንገት ኤሳው መጥቶ መርቀኝ ሲለው በድንጋጤ ክፉኛ ተንቀጠቀጠ፡፡
- ይስሃቅ በአባትነቱ ለበኩር በተገባው ምርቃት የበኩር ልጁን የመባረክ መብቱን አሳጣችው፡፡
- ያዕቆብ ኤሳው ሊያደርስበት ካሰበው ጥቃት ሸሽቶ በእግር ሁለት ሳምንታት በላይ የሚያስኬድ (800 ኪ.ሜ) መንገድ በመጓዝ እንዲሰደድና በስደት ላይ ለ20 ዓመታት ያሳለፈውን ከባድ ኑሮ አስከተለበት፣ ዘፍ 31፡38-41፡፡
- ያዕቆብ ሸሽቶ ባይሰደድ ሁለቱም ልጆችዋ በአንድ ቀን ሊያሳጣት የሚችል ነበር (ሁለቱ ቢገዳደሉ) ዘፍ 27፡45
- ኤሳው ተቆጥቶ ወንድሙን ለመግደል ወስኖ ምቹ ጊዜ እስኪያገኝ መጠባበቅ ላይ አደረሰው፡፡
- እርሷም ከዚያ በኋላ የምትወደው ልጇ ያዕቆብን በዓይኗ ማየት አልቻለችም፡፡ (ርብቃ ጊዜው በትክክል ባይታወቅም ያዕቆብ በስደት ላይ እንደ ነበረ መሞትዋ ይታመናል፡፡)

<u>የእግዚአብሔር ምርጫ</u>

እግዚአብሔር ከመንትዮቹ ልጆች የትኛው የበረታ እንደሚሆን የተስፋ ቃል ሲሰጥ ለመበርታቱ ያስቀመጠው ቅድመ-ሁኔታ የለም፡፡ ታናሹ ይበረታል ብሎ የተስፋ ቃል ሲሰጥ ይህም የሚፈጸመው አባቱ ከመረቀው ነው የሚል ወይም ሌላ ቅድመ-ሁኔታ የለም (unconditional). እግዚአብሔርም ያዕቆብን የመረጠበት ምክንያት መጀመሪያ ላይ ሆኖ ፍጻሜን ማየት የሚችል በመሆኑ አስቀድሞ ያዕቆብም ሆነ ዘሩ ፍጹም ሰዎች ባይሆኑም ከኤሳውና ከዘሩ የተሻለ መንፈሳዊ ሕይወት ያላቸው ሰዎች እንደሚሆኑ ያውቅ ስለ ነበር ነው። ይህም በሁለቱ ልጆችና በዘሮቻቸው እውን ሆኖ ታይቷል። ከያዕቆብ ዘር ታላላቅ የእግዚብሔር ሰዎች ተወልደው ታይዋል። እግዚአብሔር በምርጫው አይሳሳትም።

(ኢሳ 46፡10፣ እግዚአብሔር መጀመሪያ ላይ ሆኖ መጨረሻውን ስለሚያይ፣ ኤር 1፡4-5 "በማህጸን ሳልሰራህ በፊት አወቅሁህ፣ ከመወለድህ በፊት ለየሁህ፣ ለህዝቦችም ነብይ ትሆን ዘንድ ሾምሁህ" ስለሚል)

1 ሳሙ 15፥28፣ "ሳሙኤልም እንዲህ አለው፤ "እግዚአብሔር የእስራኤልን መንግሥት ዛሬ ከአንተ ቀዶታል፤ ከአንተም ለሚሻል ለጎረቤትህ አሳልፎ ሰጥቶታል።"

ይስህቅ ኤሳውን እንደ በኩር መርቆት ቢሆን እንኳ ያዕቆብ በሁለት ነገሮች ምክንያት የአብርሀም በረከት ወራሽ ነበር፡- 1. ብኩርናን እጅግ በመፈለጉ በመሃላ በተረጋገጠ ሁኔታ በዋጋ በመግዛቱ፡፡ በሻጩ ስምምነት በዋጋ ገዛ ማለት የዔሳው የብኩርና በረከት ወደ ራሱ እንዲዞር አደረገ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ያለሰው ፈቃደኝነት/ፍላጎት በረከትን በግዴታ በሰው ላይ ስለ ማይጭን በስምምነታቸው መሰረት ለያዕቆብ ይሰጠው ነበር፡፡

2. በእግዚአብሔር የተመረጠው እርሱ በመሆኑ፡፡ ያዕቆብ የብኩርና መብት ያገኘው እናቱ በመከረችው ምክር መሰረት ኤሳው ነኝ ብሎ ዋሽቶ በአባቱ በመመረቁ አይደለም፡፡ ዮሴፍ እግዚአብሔር የተናገረው የተስፋ ቃል በረከት የወረሰው አባቱ ስለመረቀው ወንድሞቹም እንዲባረክ ስለተስማሙ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ስለ መረጠው ነው እንጂ፡፡ እግዚአብሔር ከፍ ሊያደርገው የመረጠውን ማንም ሊለውጠው አይችልም፡፡ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ሰው እንዲመርጥና እንዲባርክ የማንም እርዳታ አያስፈልገውም፡፡ ሮሜ 9፡11

በይስሃቅ ዕድሜ መጨረሻ ላይ ቤተሰቡ ውስጥ የተፈጠረው ምስቅልቅል በማየት ማንኛውም ወንድ የሆነ ክርስቲያን ቤተሰብ አፍርቶ ዕድሜው ገፍቶ ምድራዊ ኑሮው ማብቂያ ላይ ሲደርስ ከላይ የታየው ዓይነት ችግር በቤተሰቡ ውስጥ እንዳይፈጠር ቢያንስ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይገባዋል፡፡

1. አባት የሚመርቀው ልጁን በሚመርቅበት፣ የሚያከፋፍለው ሃብትም ካለው በሚያከፋፍልበት ሰዓት ቢያንስ ሁሉም ልጆቹ ከእናታቸው ጋር እንዲገኙ ማድረግ አለበት፡፡ ያዕቆብ ልጆቹን የባረከው በዚህ ሁኔታ በመሆኑ የእርሱን የተሻለ መልካም አርአያነት ያለው ተግባር መከተል ይገባል፡፡ ዘፍ 49፡1 (ይስሃቅ ግን ኤሳውን ብቻ ሊመርቅ ተዘጋጅቶ ነበር)
2. አባት ምድራዊ ኑሮውን ሁሉ ኑሮ ፍጻሜ ላይ የደረሰ በመሆኑ መባረክ ያለበት ሁሉም ልጆቹን ነው እንጂ አንዱን ባርኮ ሌሎቹን መዘንጋት የለበትም፡፡ ስለዚህ ሁሉንም የሚባርክበት በረከት አስቦ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ኤሳው አባቱ ይስሃቅን እኔንም ባርከኝ ብሎ ሲጠይቀው ምን ብሎ እንደሚባርክ ስለ ተቸገረ "አባቴ ሆይ በረከትህ አንዲት ብቻ ናትን?" ብሎ እሰከ መጠየቅ ድረስ አደረሰው፡፡
3. ልጆቹ እርስ በርሳቸው እንዲተሳሰቡና እንዲደጋገፉ እንጂ በምንም ዓይነት እርስ በርስ እንዳይዋጉ/እንዳይጣሉ በመምከር ማሳደግና ሊሞት ሲልም እንደዚያው እንዲተባበሩ ማስገንዘብ ይኖርበታል፤
4. ከልጆቹ መካከል ያሳዘነው ሰው ካለ ይቅር ማለትና ማንኛውም የቤተሰቡ አባል ቀርቶ አላግባብ የጎዳው ከቤተሰቡ ውጪ የሆነ ሰው ቢኖር አዲሱ ኪዳን መራገምን ይከለክላል፡፡ በመጨረሻም በአንድነት የበረከት እንጀራ ቆርሰው በደስታ እግዚአብሔርን አመስግነው ማብቃት ነው፡፡

**የኛ ብኩርና፡-** በመጽሐፍ-ቅዱስ በየአካባቢው/አገሩ በወንጌል በማመን የመጀመሪያዎቹ የወንጌል አማኞች፣ ቤተሰቦች፣ ወይም ቤተክርቲያን በኩራት ተብለው ተጠርተዋል፡፡ 1ቆሮ 16፡15፣ ዕብ 12፡22-23፣ ሮሜ 16፡5፡፡

ስለዚህ አገራችን የወንጌል እምነት የተስፋፋባት አገር ስላልሆነች እኛ እያንዳንዳችን ጌታን አምነን በዳንንበት አካባቢ ከመጀመሪያዎቹ አማኞች የምንቆጠር ብዙዎች ስላለን ለእግዚአብሔር እንደ በኩራት ነን፡፡ ስለዚህ እያንዳንዳችን የበኩርን ሚና በመጫወት አዲስ የዳኑት አማኞችን እንደ አስፈላጊነቱ እንደየችሎታችን በመደገፍ፣ በውጪ ያሉት እንዲድኑ በቃልና በመልካም አርአያነት ምስክር በመሆን ለወንጌል መሰፋት በተቻለን መጠን ብንሰራ እግዚአብሔር የብኩርናን በረከት ያጎናጽፈናል፡፡ ክብር ለስሙ ይሁን አሜን!!